ፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር
የባለአክሲዮኖች 26ኛ መደበኛ ጉባኤ

ጠቅላላ ጉባዔው የተደረገበት ቦታ፣ ቀንና ሰዓት

ቦታ፡- ፒስ ማይክሮፋይናንስ ዋናው መ/ቤት (አዲስ አበባ)
ቀን፡- ታህሳስ 15, 2015 ዓ.ም.
ሠዓት፡- ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 6፡30

2. የጉባኤው ጥሪ አደራረግ፣

ይህ የባለአክሲዮኖች 26ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተጠራው በንግድ ህግ አንቀጽ 370 መሠረት ሆኖ ከጉባዔው ዕለት 24 ቀናት አስቀድሞ በደብዳቤ ቁጥር PEACE/651/22 በ ኖቬምበር 26/2022 በተፃፈ እና በአድራሻ በተላከ ደብዳቤ በተጨማሪም በስልክ ተጠርተዋል፡፡

3. ድምፅ ቆጣሪዎች፣ የማሕበሩ ፀሐፊና የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት

3.1 ሰብሳቢ፣ ድምፅ ቆጣሪዎች እና የማህበሩ ፀሐፊ

በንግድ ህግ አንቀፅ 379 መሠረት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት አቶ ጌታቸው ወርቁ የጉባኤው ሰብሳቢ ሲሆኑ፣ በንግድ ህግ አንቀጽ 380(1) መሠረት የጉባዔው ድምጽ ቆጣሪ በስብሰባው ከተገኙት ባለ አክሲዮች ከፍተኛ ድርሻ ባላቸው ባለአክሲዮኖች መካከል በተደረገ ስምምነት መሠረት፡-

1ኛ. ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ
2ኛ. አቶ ኤፍሬም አላምረው የጉባኤው ድምጽ ቆጣሪ እንዲሆኑ ተስማምተዋል፡፡
ወ/ሮ አዜብ በቀለ በንግድ ህጉ አንቀጽ 340 መሠረት ቋሚ የማህበሩ ፀሐፊ ናቸው፡፡

| ተ/ቁ | ስም | ኃላፊነት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ | የጉባኤው ሰብሳቢ |
| 2 | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ | ድምጽ ቆጣሪ |
| 3 | አቶ ኤፍሬም አላምረው | ድምጽ ቆጣሪ |
| 4 | ወ/ሮ አዜብ በቀለ | የማህበሩ ፀሐፊ |

3.2 በጉባኤው የተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣

| ተ/ቁ | ሥም | ተወካይ ከሆነ የተወካይ ሥም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | - | የቦርድ ሰብሳቢ | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | - | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | - | የቦርድ አባል | |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | - | የቦርድ አባል | |
| 5 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | - | የቦርድ አባል | |
| 6 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | ወ/ሮ ዓይናለም አሸብር | የቦርድ አባል | |

3.3 በጉባኤው ያልተገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣

የለም

3.4 በጉባዔው የተገኘ ታዛቢዎች፤

| ተ/ቁ | ስም | የወከሉት ድርጅት |
|---|---|---|
| 1 | አቶ አመሃ ተካ | የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ |

3.5 በጉባዔው የተገኙ ኦዲተር

ቲ. ኤ. ዋይ የተፈቀደላቸው የሒሳብ አዋቂዎችና ኦዲተሮች - ተወካይ ወ/ሪት ትዕግስት በየነ

4. ምልዓተ ጉባኤ፤

4.1. ጠቅላላ የማኅበሩ አባላት ብዛት 16

4.2. ጠቅላላ የማኅበሩ የተፈረመ አክስዮን ብዛት 30,324

4.3. በስብሰባው የተገኙ አባላት ብዛት 13 የያዙት አክስዮን ብዛት 27,662 (91.22%)

4.4. በስብሰባው ያልተገኙ አባላት ብዛት 3 የያዙት አክስዮን ብዛት 2,662 (8.78%)

4.5. ለጉባኤው አስፈላጊ የሆነ የአክስዮን ብዛት 7,581 (25%)

በዚሁ መሠረት ከማሕበሩ ባለአክሲዮኖች ከ25% በላይ የሚወክሉ አባላት የተገኙ ስለሆነ በንግድ ህጉ አንቀፅ 398 መሠረት በጉባኤው አጀንዳ ላይ ተወያይተው ውሳኔ ማሳለፍ ሥልጣን ያላቸው መሆኑ በድምፅ ቆጣሪዎች ተረጋግጦ ጉባኤው ቀጥሏል። በጉባኤው ላይ የተገኙትንና ያልተገኙትን ባለአክሲዮኖች ስም ዝርዝር እና የያዙትን አክስዮን መጠን የያዘ ሠንጠረዥ (Attendance Sheet) ከዚህ ቃለ-ጉባዔ ሰነድ ጋር ተያይዟል።

5. የጉባዔው አጀንዳዎች

5.1. የጉባኤው ረቂቅ አጀንዳ ማፅደቅ፤
5.2. እ.ኤ.አ. የ2021/2022 የዳሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤
5.3. እ.ኤ.አ. የ2021/2022 የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤
5.4. የአክሲዮን ማህበሩን የሂሳብ ሚዛን ማጽደቅ፤
5.5. በማህበሩ የተጠራቀመ ትርፍና እ.ኤ.አ. በ2021/22 የተገኘ ትርፍ ላይ ተወያይቶ ወደ ካፒታል ማዞር፤
5.6. የአክስዮን ዝውውር ማጽደቅ፤
5.7. በለቀቁ ዳይሬክተሮች ምትክ የአዲስ አባላት ሹመት ማጽደቅ፤
5.8. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ ናቸው፡፡

6. የጉባኤው ውይይት አጭር ቃልና ውሣኔ፣

6.1. አጀንዳ 5.1 የጉባኤው ረቂቅ አጀንዳ ማጽደቅ

6.1.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጉባኤው ሰብሳቢ ጉባኤው ሊነጋገርባቸው ይገባል በማለት የቀረቡትን ረቂቅ አጀንዳዎች በንግድ ሕጉ መሠረት እንደሆኑ በማስረዳት አጀንዳዎቹም በመደበኛ ጉባዔ የሚታዩ መሆናቸው ተገልጾ ጠቅላላ ጉባኤው የአጀንዳውን አስፈላጊነት ተገንዝቦ እንዲያጸድቅ ተጠይቋል፡፡

6.1.2 ውሣኔ፣

የቀረቡት አጀንዳዎች የመደበኛ ጉባኤ አጀንዳዎች በመሆናቸው የአክስዮን ማሕበሩ አባላት በሙሉ ድምጽ አጽድቀው ስብሰባው ተጀምሯል፡፡

6.2 አጀንዳ 5.2. እ.ኤ.አ. የ2021/2022 የዳሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤

ለጉባኤው የቀረበ የዳሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት

የዳሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የ2021/22 በጀት አመት ሪፖርቱን በዝርዝር ለጠቅላላ ጉባኤው በንባብ አሰምተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሪፖርቱ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

የሪፖርቱም ይዘት በበጀት ዓመቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሥራ አመራር ያደረጓቸው ስብሰባዎችና ያስተላለፏቸው ውሳኔዎች፤የቁጠባና የብድር አፈጻፀም ሪፖርት ይዘት፣ የተቋሙ የሰው ኃብት ያለበትን ደረጃ፣ የተቋሙን የሀብት ሚዛን መግለጫ፣ የትርፍና ኪሳራ ሒሳብ መግለጫ፣ የቁጠባና የብድር አፈጻፀም ሪፖርት ይዘት፣ የተቋሙ አካዳሚያዊና ማህበራዊ

ፋይዳዎች፣ የብድር ፈንድ ችግሮች እና ችግሮቹን ለመፍታት በማኔጅመንቱ እና በቦርዱ የተደረጉ ጥረቶች እና ስኬቶች፣ የተቋሙ ዋና ዋና ጠንካራ ጎኖችና መልካም አጋጣሚዎች፣ የተቋሙ መሠረታዊ ተግዳሮቶች እና ተግዳሮቶችን ለመፍታት እየተደረጉና እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቧል፡፡

- በበጀት ዓመቱ የዳይሬክተር ቦርድ አራት (4) መደበኛና ሰባት (7) መደበኛ ያልሆኑ ስብሰባዎችን አድርጓል፡፡ በእነዚህም ስብሰባ ከስልሳ በላይ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቷል፡፡
- የብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚያዘው መሰረት ቦርዱ የኩባንያው የየሩብ ዓመት የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ገምግሞ አፅድቋል፡፡
- የውስጥ ኦዲተርና የሪስክ አስተዳደር እና ኮምፕሊያንስ የየሩብ ዓመት ሪፖርት ሰምቶ ገምግሞ አፅድቋል፡፡
- የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች ቁጥር አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በድርጅቱ እየተፈጠሩ ያሉ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ቦርዱ የተቋሙ ባለቤትነትን ችግር (Ownership Challenge) ጥናት እንዲደረግ ለማኔጅመንቱ አቅጣጫ የሰጠ ሲሆን በዚህም መሠረት ከብሔራዊ ባንክ ጋር ከመወያየት ጀምሮ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡
- በቦርድ አባላት የተቋቋሙት ንዑሳን ኮሚቴዎች ማለትም ቁጥጥር እና ስጋት አስተዳደር ኮሚቴ እና ሀብት እና ዕዳ አስተዳደር ኮሚቴ ዝርዝር ሪፖርት ተነጋግሮበታል፡፡

<u>የቁጠባ ዕቅድ እና አፈጻጸም</u>

- የቁጠባ ተደራሽነት ዕቅድ 116,000 ደንበኞች ሲሆን አፈፃፀሙ 107,244 (92% አፈፃፀም) ከእነዚህም ውስጥ 55% ወይም 58,957 የሚሆኑት ሴቶች ናቸው፡፡
- ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት (95,791) ጋር ሲነጻጸር የ12 በመቶ (11,453) ደንበኞች ጭማሪ አሳይቷል፡፡
- በዓመቱ ጠቅላላ ከደንበኞች ሊሰበሰብ የታቀደው የቁጠባ መጠን ብር 160,600,000 ሲሆን አፈፃፀሙ ብር 169,643,075 (106%) ነው፡፡ ካለፈው ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የ 37.3% ወይም ብር 46,104,155 ጭማሪ አሳይቷል፡፡
- በዓመቱ ጠቅላላ ከደንበኞች ሊሰበሰብ የታቀደው የቁጠባ መጠን ብር 160,600,000 ሲሆን አፈፃፀሙ ብር 169,643,075 (106%) ነው፡፡ ካለፈው ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የ 37.3% ወይም ብር 46,104,155 ጭማሪ አሳይቷል፡፡
- የለነገ ህጻናትና ወጣቶች በዓመቱ የቆጠቡት የብር መጠን 26,026,799 ሲሆን ከጠቅላላው የቁጠባ መጠን 15% ይይዛል፡፡

የደንበኞች የቁጠባ ባላንስ እቅድ መጠን ብር 177,598,683 ሲሆን አፈፃፀሙ የባላንስ መጠን ብር 168,196,531 ወይም (95%) ነው። ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ30% ወይም ብር 39,166,250 ጭማሪ አሳይቷል

## የደንበኞች የብድር ተደራሽነት ቁጥር ዕቅድ አፈፃፀም

- የዓመቱ የተበዳሪ ደንበኞች ተደራሽነት ዕቅድ 38,280 ነው፡፡
- አፈፃፀሙ 31,584 (82.5%) ሲሆኑ ከዚህም ውስጥ 22,225 (70.4%) የሚሆኑት ሴቶች ናቸው:

## የብድር ስርጭት ዕቅድና አፈፃፀም

- የዓመቱ ለደንበኞች የብድር ስርጭት ዕቅድ ብር 516,148,000 ሲሆን አፈፃፀም ብር 520,648,700 ነው (101% አፈፃፀም) ፡፡

## የብድር ፖርትፎሊዮ ይዘት

- እስከ ሰኔ 30 ቀን 2022 ድረስ በደንበኞች እጅ ያለው ብድር ብር 527,303,825 ነው።
- በአጠቃላይ በበጀት አመቱ ብር 351,372,556 ከደንበኞች የተሰበሰበው ነው።

## የብድር ጥራት ምዘና

- በፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ ደንብ መሠረት ከአንድ ቀን ጀምሮ በጊዜው ያልተመለሰ የብድር መጠን (PAR greater than one day) 5.91% ሲሆን እንደ ብሔራዊ ባንክ መለኪያ ደግሞ (PAR greater than Ninety days) 3.36%፡፡

## አነስተኛ የብድር የህይወት መድን ሽፋን

- በበጀት ዓመቱ ከአነስተኛ የብድር የህይወት መድን ሽፋን ጠቅላላ ከደንበኞች የተሰበሰበ ብር 4,240,362 ሲሆን ከዚህም ውስጥ ብር 467,315.64 ለሟች ደንበኞች ብድር ማካካሻ ተረርጓል፡፡

## የሰው ሃይል ሀብት

- እ.ኤ.አ ጁን 30, 2021 ድረስ አጠቃላይ የሠራተኞች ቁጥር 341 ነው።
- ከዚህም ውስጥ የዋናው ቢሮ ሰራተኞች ቁጥር - 38(11%) ሲሆን የቅርንጫፍ ሰራተኛ ቁጥር 303 (89%)ነው።
- የሴት ሰራተኞች ቁጥር 55(16%) ሲሆን የወንድ ሰራተኞች ቁጥር ደግሞ 286(84%) ነው።
- የሴት ሠራተኞች ቁጥር ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

**ተቋሙ የሀብት ሚዛን**

እ.ኤ.አ ጁን 30, 2022 መጨረሻ ድረስ የድርጅቱ አጠቃላይ ሀብት ብር 682,635,690 ሲሆን 77.3% (527,827,362)፡፡ ካለፈው ዓመት የ loan portfolio ጋር ሲነፃፀር የ46% ዕድገት አሳይቷል፡፡

- ከጠቅላላው loan portfolio ውስጥ 42% የሚሆነው ለግብርና የተሰጠ ብድር ሲሆን የተቀረው 58% ከግብርና ውጭ ላሉ የስራ ዓይነቶች የተሰጠ ብድር ነው፡፡
- ጠቅላላ የድርጅቱ ዕዳ 544,155,571 ብር ሲሆን ከዚህም ውስጥ 31% የሚሆነው የተበዳሪዎች ቁጠባ፣ 41% የልማት ባንክ (RUFIP) ብድር፣ 11% የኦሮሚያ ኢንተርናሽናል ባንክ ብድር፤ 1% የኦሮሚያ ህብረት ሥራ ባንክ ብድር; 7% የአዋሽ ባንክ ብድር እንዲሁም 2% የዩኤንሲዲኤፍ (UNCDF) ናቸው፡፡
- ጠቅላላ የድርጅቱ ካፒታል ብር 138,480,119 ሲሆን ከዚሁም ውስጥ ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የተጠራቀመ የድርጅቱ ትርፍ ነው፡፡ ይሄም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር የ24% ጭማሪ አሳይቷል፡፡

**የዓመቱ የተጣራ ትርፍ**

- በበጀት ዓመቱ ተቋሙ ያተረፈው የተጣራ ትርፍ ብር 21,151,105 (ሃያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺህ አንድ መቶ አምስት ብር) ፡፡

**ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች**

- ተቋሙ ለደንበኞቹ በሚሰጠው አገልግሎት ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ለመገምገም በተደረገው ጥናት ቁጥራቸው 10,782 የሚሆኑ ከተቋሙ ለሁለተኛ ዙርና ከዚያ በላይ ከተበደሩ ደንበኞች መካከል የደንበኞች ዳሰሳ ጥናት ተደርጓል በዚህም መሠረት
  - 7734 (72%) የሚሆኑት ሀብት መፍጠር እንደቻሉ፤
  - 2368 (22%) የሚሆኑት የምግብ ዋስትናና የተሻለ የህክምና አገልግሎት ማረጋገጥ እንደቻሉ
  - 680 (6%) የሚሆኑት ደግሞ የልጆቻቸውንና የራሳቸውን የትምህርት ቤት ክፍያ መክፈል እንዳስቻላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ከላይ ቁጥራቸው ከተገለፀው ጥያቄ ከቀረበላቸው ደንበኞች ውስጥ አብዛኞቹ በማህበራዊ ህይወታቸው ተቀባይነት እንዳገኙና በራስ መተማመናቸው እንደጨመረ አስረድተዋል፡፡
- በተጨማሪም 99% የሚሆኑት የተቋሙ የብድር አገልግሎት እጅግ እንደረዳቸው ሲገልፁ 1% የሚሆኑት ደግሞ የብድር አገልግሎቱ ምንም ወይም በጥቂቱ ብቻ እንደረዳቸው ገልጸዋል፡፡

### ደንበኞችን በተመለከተ

- በበጀት ዓመቱ 9,415 ደንበኞች የለቀቁ ሲሆን ካለፈው ዓመት ጋር ሲነፃፀር በ9% ቅናሽ አሳይቷል።

**የለቀቁበት ምክንያት**

- 19.5% በንግድ ምክንያት፤
- 37.2% የሚሆኑት የተቋሙ የብድር ፖሊሲ አመቺ ባለመሆኑ፤
- 31.9% የሚሆኑት በቡድን የብድር አሰራር መሠረት፤
- 3.74% በአካባቢያዊ አለመመቸት እና ኢኮኖሚያዊ ጫና ምክንያት እና
- 7.7% የሚሆኑት በራሳቸው የግል ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል።

**<u>የተቋሙ ዋና ዋና ጠንካራ ጎኖችና መልካም አጋጣሚዎች</u>**

- የተቋሙ ሥራ አመራር ቦርድ በየወሩ መደበኛ ስብሰባ እየተሰበሰበ ጠንካራና ስትራቴጂክ አቅጣጫዎችን እየሰጠ ይገኛል፡፡
- ተቋሙ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር መልካም የስራ ግንኙነቶችን በመፍጠር ወደፊት ተቋሙን ሊጠቅሙ የሚችሉ መልካም አጋጣሚዎችን መፍጠር መቻሉ፡፡
- ተቋሙ አገልግሎቱን ለማዘመንና የ MIS ችግር ለመፍታት በአሁን ሰዓት ከሌሎች ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር Shared MIS መጠቀም በሚያስችል ሁኔታ እየሰራ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በተቋሙ (Management Information System-MIS) ኮር ባንኪንግ 32 ቅርንጫፎችን በቀጥታ (online) ከዋናው መ/ቤት ጋር በማገናኘት የቀን በቀን ስራዎቻቸውን መከታተል ተችሏል፡፡
- የተቋሙ አጠቃላይ የብድር መጠንና የሚያገለግላቸው ደንበኞች ቁጥር በማደግ ላይ መገኘቱ፤

**የተቋሙ ዋና ዋና ተግዳሮቶች ፡-**

- ለብድር አገልግሎት የሚውል ገንዘብ እጥረት፤
- በተለያዩ ምክንያቶች የደንበኞች እና የሠራተኞች ከተቋሙ መልቀቅ፤
- በበጀት አመቱ እንደሚታወቀው በነበረው የአካባቢ የፀጥታ ሁኔታ በስራዎቻችን ላይ ጫና መፍጠሩ ማለትም የተቋሙ የብድርም ሆነ የቁጠባ እድገት ላይ እክል ገጥሞታል ።
- የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች ቁጥር አነስተኛ በመሆኑ ድርጅቱ የብሔራዊ ባንክን መስፈርት እንኳን ለማሟላት ተግዳሮት ሆኖበታል በዚህም ምክንያት የህብት እና ዕዳ አስተዳደር ኮሚቴ በሰው ሀይል እጥረት ምክንያት እክል ገጥሞታል።
- በተጨማሪም በአዲሱ የብሔራዊ ባንክ ዳይሬክቲቭ መሠረት የኦዲት ቻርተር ፖሊሲ መሠረት የቦርዱ የኦዲት ኮሚቴ ለማቋቋም አልተቻለም።

ቀጥሎ ለመቆጣጠር እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች

- ለበዩር የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት ድርጅቱ ከንግድ ባንኮች፣ ከተለያዩ ለጋሽ ተቋማትና ከመንግስት ባንኮች ብድር በማፈላለግ ችግሩን ለመቅረፍ ጥረት አድርጓል።

- በአሁኑ ወቅትም ከተለያዩ ባንኮች እና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር የገንዘብ ምንጭ ለማግኘት ጥረት እየተደረገ ነው።

- የድርጅቱ ባለአክሲዮኖች ቁጥር አነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በድርጅቱ እየተፈጠሩ ያሉ ተግዳሮቶች ለመቅረፍ ቦርዱ የተቋሙ ባለቤትነትን ችግር /Ownership Challenge/ ጥናት እንዲደረግ ለማኔጅመንቱ በሰጠው አቅጣጫ መሠረት ጥናት ያስጠና ሲሆን በተጨማሪም ከብሔራዊ ባንክ ጋር መወያየትን ጨምሮ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረገ ይገኛል።

- የፀጥታ ችግር ላስከተለው ተፅዕና ምላሽ ለመስጠት ቦርዱ ትኩረት ሰጥቶ ስብሰባዎችን በማካሄድ አቅጣጫ እየሰጠ የሚገኝ ሲሆን በማኔጅመንት ደረጃም ኮሚቴ ተቋቁሞ በየሳምንቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቻችን መረጃ በመሰብሰብ ለችግሩ የመፍትሄ አቅጣጫ እየተሰጠ ይገኛል።

6.2.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የውጭ ኦዲተሮች በቦርዱ የቀረበውን ሪፖርት ትክክለኛነት ለጠቅላላ ጉባኤው ካረጋገጡ በኋላ ጠቅላላ ጉባዔ አባላት በቀረበው ሪፖርት ላይ ተወያይቶ ቦርድ ሪፖርትን ለጠቅላላ ጉባኤው ለውሳኔ አቅርቧ፡፡

6.2.1.1 ውሣኔ

በቀረበው የዳሬክተሮች ቦርድ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ጉባዔው በመነጋገር አፈጻጸሙ አጥጋቢ እንደነበር በመግለጽ ጉባኤው የዳሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

## 6.3 አጀንዳ 5.3 እ.ኤ.አ. የ2021/2022 የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፤

6.3.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የውጪ ኦዲተር ቲ.ኤ.ዋይ. የተፈቀደላቸው የሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች የተቋሙን የ2021/22 በጀት ዓመት የሒሳብ መግለጫ በአለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት አዘገጃጀት/IFRS/ መሠረት በጽሑፍ አቅርቧል፡፡ በዚህም መሠረት የኃብት እና ዕዳ መግለጫ፣ የገንዘብ ፍሰት መግለጫ፣ የድርጅቱን የተጣራ ኃብት መግለጫ፤ በዝርዝር በማብራራት የድርጅቱ የሂሳብ አካሄድ በሂሳብ መርማሪዎች አመለካከት አለም አቀፍ የሂሳብ አያያዝን የተከተለ እና ተቀባይነት ባለው መሠረታዊ የሂሳብ አያያዝ መስፈርት የተሟላ መሆኑን የውጭ ኦዲተሩ ቲ.ኤ.ዋይ. የተፈቀደላቸው የሂሳብ አዋቂዎች እና ኦዲተሮች ገልጸው የተቋሙን የኦዲት ሪፖርት ለጉባኤው አስደምጠዋል።

በሪፖርቱ እ.ኤ.አ ጁን 30, 2022 መጨረሻ ድረስ የድርጅቱ ጠቅላላ ሀብት ብር 682,635,690 (ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሚሊየን ስድስት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ.ህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር) መሆኑ ተጠቅሶ የተቋሙ ገቢ ከባለፈው በጀት አመት ጋር ሲነጻጸር መጨመሩን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም የብድርና የቁጠባ መጠን መጨመሩን ተጠቅሶ ጠቅላላ ጉባኤው የቀረበውን የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ካደመጠ በኋላ ሪፖርቱ በግልጽ ሁኔታ በመቅረቡ ከጠቅላላ ጉባዔው ምንም አይነት የማብራሪያ ጥያቄ ባለማቅረቡ የኦዲት ሪፖርትን ለማጽደቅ ለውሳኔ ቀርቧል፡፡

6.3.2 ውሣኔ

ጉባኤው የተቋሙን የ2021/22 የውጪ ኦዲተሮች ሪፖርት ካደመጠ በኋላ ሪፖርቱን በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

## 6.4 አጀንዳ 5.4 የአክሲዮን ማህበሩን የሂሳብ ሚዛን ማጽደቅ፤

### 6.4.1 የውይይቱ አጭር ቃል

እ.ኤ.አ ጁን 30, 2022 መጨረሻ ድረስ የድርጅቱ ጠቅላላ ሐብት ብር 682,635,690 (ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሚሊየን ስድስት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ.ህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር) ሲሆን ከዚህም ውስጥ 77.3% (527,827,362) የሚሆነው በተበዳሪዎች እጅ የሚገኝ ገንዘብ (loan portfolio) ነው ፡፡ ካለፈው ዓመት የ loan portfolio ጋር ሲነፃፀር የ46% እድገት አሳይቷል፡፡

### 6.4.2 ውሣኔ

የድርጅቱ ጠቅላላ ሐብት (Total Asset) ብር 682,635,690 (ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ሚሊየን ስድስት መቶ ሰላሳ አምስት ሺ.ህ ስድስት መቶ ዘጠና ብር) ሲሆን ጠቅላላ የድርጅቱ የተጣራ ካፒታል ብር 138,480,119(አንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ሚሊየን አራት መቶ ሰማንያ ሺ.ህ አንድ መቶ አስራ ዘጠኝ ብር) ሲሆን ከዚሁም ትልቁን ድርሻ የሚይዘው ባለፉት ተከታታይ ዓመታት የተጠራቀመ ትርፍ መሆኑ ከተነጋገሩበት በኋላ በሙሉ ድምጽ አፅድቋል፡፡

## 6.5 አጀንዳ 5.5 በማህበሩ የተጠራቀመ ትርፍና እ.ኤ.አ. በ2021/22 የተገኘ ትርፍ ላይ ተወያይቶ ወደ ካፒታል ማዞር፤

### 6.5.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የማህበሩ 9ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ህዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም የማህበሩ ካፒታል ከብር 30,324,000 (ሰላሳ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ አራት ሺ.ህ ብር) ወደ 100,000,000 (አንድ መቶ ሚሊዮን ብር) እንዲያድግ በወሰነው መሠረት ከማህበሩ የተጠራቀመ ትርፍ ብር 34,036,000

(ሰላሳ አራት ሚሊዮን ሰላሳ ስድስት ሺ.ህ ብር) እንዲሁም የማህበሩ እ.ኤ.አ የ2021/22 በጀት ዓመት ትርፍ ብር 21,151,105 (ሃያ አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ አንድ ሺ.ህ አንድ መቶ አምስት ብር) ላይ በማሕበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 7(ሐ) መሰረት 2,115,110.50 (10%) ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ እንዲተላለፍ ተደርጎ ቀሪው 19,035,994.50 (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰላሳ አምስት ሺ.ህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከ50/100) ለአባላት ያልተከፈለ አክሲዮን ክፍያ እንዲውልና የማህበሩም ያልተከፈለ ካፒታል እንዲያድግ በሚለው ላይ ጉባዔው ተወያይቶበታል፡፡

በመሆኑም እስከ ጁን 30,2022 ሂሳብ መዝጊያ ከተጠራቀመው ትርፍና እ.ኤ.አ ከ2021/2022 በጀት ዓመት ትርፍ ብዛታቸው 53,068 (ሃምሳ ሶስት ሺ.ህ ስልሳ ስምንት) የሆኑ ተፈርመው ያልተከፈሉ አክሲዮኖች እንዲከፈል በሚለው ላይ ጉባዔው ተወያይቶበታል፡፡

በተጨማሪም ከዚ.ህ በፊት በስህተት የአክሲዮናቸው ድርሻቸው ሳያድግላቸው የተዘለሉ ባለአክሲዮኖች በዕዳ ተመዝግቦ ከነበረው ትርፋቸው ተወስዶ ድርሻቸው ተጨምሮ እንዲደለደል ጉባዔው ተወያይቶበታል፡፡

6.5.2 ውሳኔ

ጉባዔው እስከ ጁን 30 2021 ሂሳብ መዝጊያ የተጠራቀመውን ትርፍ ብር 34,036,000 (ሰላሳ አራት ሚሊዮን ሰላሳ ስድስት ሺ.ህ ብር) እንዲሁም የ2021/22 ሂሳብ ዓመት ትርፍ ብር 21,151,105 10% ወደ ህጋዊ መጠባበቂያ ሂሳብ ከተላለፈ በኂላ ቀሪው ብር **19,035,994.50** (አስራ ዘጠኝ ሚሊዮን ሰላሳ አምስት ሺ.ህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከ50/100) የባለአክሲዮኖችን የተከፈለ ካፒታል በማሳደግ የማህበሩን የተከፈለ ካፒታል እንዲያድግ፣ በዚሁ መሠረት እያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺ.ህ ብር) ዋጋ ያላቸው ብዛታቸው 53,068 (ሃምሳ ሶስት ሺ.ህ ስልሳ ስምንት) የተፈረሙ አክሲዮኖችን ዋጋ በመክፈል የማህበሩ የተከፈለ ካፒታል ከብር 30,324,000 (ሰላሳ ሚሊዮን ሶስት መቶ ሃያ አራት ሺ.ህ ብር) ወደ ብር 83,392,000 (ሰማንያ ሶስት ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና ሁለት ብር) የተከፈለ ካፒታል እንዲያድግ ጉባዔው በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡

በተጨማሪም ወደ ካፒታል የሚዞረው ትርፍ ድልድል ባለአክሲዮኖች ባላቸው የአክሲዮን መጠን መሠረት እንዲሆን በሙሉ ድምጽ ወስኗል፡፡ እንዲሁም የአክሲዮን ድርሻቸው ሳያድግላቸው የቀሩ ባለአክሲዮኖች ከዕዳ ከተመዘገበው ትርፋቸው መጠን በወቅቱ በነበራቸው አክሲዮን ድርሻቸው እንዲደለደል ተወስኗል፡፡

| ተ.ቁ | የባለ አክሲዮን ስም | የተከፈ ካፒታል በብር | ሼር ላደረጉላቸው የታለፉ ባለአክሲዮኖች በፀደ ከተመዘገበ ተቀንሶ ትርፍ ድርሻቸው የተጨመረላቸው | የተከፈ ካፒታል + ሼር ላደረጉላቸው የታለፉ ባለአክሲዮኖች በፀደ ከተመዘገበ ተቀንሶ ትርፍ ድርሻቸው የተጨመረላቸው | እስከ ጁን 30/2021 የሂሳብ መዝገብ በፀደ የተመዘገበ ትርፍ ድርሻ በብር | የ2021/22 ሂሳብ ዓመት ትርፍ ድርሻ በብር | በፀደ የተመዘገበ + የ2021/22 ትርፍ ድልድል በብር | ጠቅላላ የተጨመረ አክሲዮን በቁጥር | ጠቅላላ የተጨመረ አክሲዮን በብር | ከትርፍ ድልድል በኋላ በፀደ የተመዘገበ ቀሪ ድርሻ በብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሸንቁጥ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | 2,452,000.00 | 48,000.00 | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,760,249.66 | 2,760.25 | 2,760,000.00 | 249.66 |
| 5 | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መኮተ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 6 | ወ/ሮ ለበሰች ጸጋ ባለህ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 7 | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 8 | ወ/ሮ ጽለምንሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 9 | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 10 | አቶ ብዙአየሁ ከበደ በቀለ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 11 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | 129,000.00 | 2,371,000.00 | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 5,083,249.66 | 5,083.25 | 5,083,000.00 | 249.66 |
| 12 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ስሜነው | 81,000.00 | 2,419,000.00 | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 5,131,249.66 | 5,131.25 | 5,131,000.00 | 249.66 |
| 13 | ሲ/ር መሠረት ሺፈራው ይብራሁ | 81,000.00 | 2,419,000.00 | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 5,131,249.66 | 5,131.25 | 5,131,000.00 | 249.66 |
| 14 | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | 81,000.00 | 2,419,000.00 | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 5,131,249.66 | 5,131.25 | 5,131,000.00 | 249.66 |
| 15 | ወ/ት ፍላጐት ለማ ክብረት | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| 16 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | 2,500,000.00 | - | 2,500,000.00 | 1,522,500.00 | 1,189,749.66 | 2,712,249.66 | 2,712.25 | 2,712,000.00 | 249.66 |
| | ድምር | 30,324,000.00 | 9,676,000.00 | 40,000,000.00 | 24,360,000.00 | 19,035,994.50 | 53,071,994.50 | 53072 | 53,068,000.00 | 3,994.50 |

## ፩.6 አጀንዳ 5.6 የአክሲዮን ዝውውር ማጽደቅ

### 6.6.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የማህበሩ ባለአክሲዮን የሆኑት ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ ያላቸውን አክሲዮን ግማሹን (50%) ለአግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ ግማሹን (50%) ለፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ በስጦታ አስተላልፈው ማህበሩን የለቀቁ መሆናቸውን በቀን ነሐሴ 5 ቀን 2014ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቁ መሆኑ ተገልጾ ይህንን የአክሲዮን ዝውውር ጉባዔው እንዲያጸድቅ ተጠይቋል፡ ጉባዔውም ተወያይቶበታል፡፡

### 6.6.2 ውሳኔ

ጉባዔው ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ለአግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ ያላቸውን የአክሲዮን ድርሻ ግማሹን (50%) እንዲሁም ለፒስ ማይክሮፋይናንስ ግማሹን (50%) በስጦታ ያስተላለፉትን ተቀብሎ የተደረገውን የአክሲዮን ዝውውር አጽድቋል፡፡

## 6.7 አጀንዳ 5.7 በለቀቁ ዳይሬክተሮች ምትክ የአዲስ አባላት ሹመት ማጽደቅ፤

### 6.7.1 የውይይቱ አጭር ቃል

የጠቅላላ ጉባዔው ቁጥር አነስተኛ መሆኑ ተጠቅሶ የቦርድ አባል ለመተካት አስቸጋሪ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑ ተጠቅሶ የቦርድ አባል የሆኑት ወ/ሮ ፀሃይ ፀጋዬ በመልቀቃቸው ቦርዱ በንግድ ህጉ አንቀጽ 303 መሠረት ፍቃደኝነታቸው ተጠይቆ አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ ወ/ሮ ፀሐይ ፀጋዬ ተክተው የቦርድ አባል ሆነው እንዲያገለግሉ የተደረገ መሆኑን ተገልጿል፡፡

ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ በራሳቸው ፍቃድ ያላቸውን የአክሲዮን ድርሻ ለአግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ ግማሹን (50%) እንዲሁም ለፒስ ማይክሮፋይናንስ ግማሹን (50%) በስጦታ በማስተላለፍ ከአባልነት የለቀቁ በመሆኑ ቦርድ አባል ሆነው ማገልገል የማይችሉ በመሆኑ በምትካቸው የቦርድ አባል እንዲሾም ተጠይቋል፡፡ በዚሁ መሠረት ካሉት ባለአክሲዮኖች ፍቃደኛ ሆነው የተገኙት አቶ ኤፍሬም አላምረው ሲሆኑ እሳቸውም አዲስ አበባ መዘዋወራቸውን ገልጸው የመስራትም ፍላጐት እንዳላቸው ለጉባኤው በማሳወቃቸው በዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ምትክ የቦርድ አባል ሆነው እንዲሾሙ ለጉባኤው ቀርቧል፡፡

የተተኪዎች የሥራ ዘመን የሚያበቃው በጎደሉት የሥራ ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ጉባዔው የአቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚን ሹመት እንዲያጸድቅ ተጠይቋል፡፡

### 6.7.2 ውሳኔ

ጉባዔው አቶ አክሊሉ ታደሰ ወ/ሮ ጸሀይ ጸጋዬን ተክተው የቦርድ አባል እንዲሆኑ በመስማማት ሹመታቸውን በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡ በተጨማሪም ጉባዔው የአቶ ኤፍሬም አላምረውን የቦርድ አባልነት ሹመት በሙሉ ድምጽ አጽድቋል፡፡

## 6.7 አጀንዳ 5.7 የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ

### 6.7.1 የውይይቱ አጭር ቃል

ታህሳስ 15/2015 ዓ.ም በተደረገው የፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ ጠቅላላ ጉባኤ፣ ጉባኤው የተነጋገረበትን ቃለ ጉባኤ በዝርዝር ተመዝግቦ በእያንዳንዱ በጉባኤው በተገኘ አባል ተፈርሞ እንዲቀመጥ ወስኗል፡፡

6.7.2 ውሣኔ

ጠቅላላ ጉባኤው ቃለ-ጉባኤው ከተነበበለት በኋላ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

7. ለጉባኤው የቀረቡ ሰነዶች
   7.1 የዳሬክተሮች ቦርድ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት
   7.2 እ.ኤ.አ የ2021/22 የተቋሙ የውጪ ኦዲተሮች የሂሳብ ሪፖርት
   7.3 የአክሲዮን ድልድል የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ

8. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የማህበሩ ጸሐፊ ማረጋገጫ

በንግድ ህጉ አንቀፅ 387(1) መሰረት እኛ የፒስ ማይክሮፋይናንስ አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት እና የአክሲዮን ማህበሩ ፀሀፊ ከዚህ ቃለ - ጉባኤ ሠነድ ጋር አባሪ ሆኖ በተያያዘው የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance Sheet) ላይ በስማቸው ትይዩ የፈረሙ ባለአክሲዮኖች በ 15 ቀን በ ታህሳስ ወር በ 2015 ዓ.ም በተካሄደው የአክሲዮን ማህበሩ 26ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ራሳቸው ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ተገኝተው በዚህ ቃለ-ጉባኤ ሠነድ ላይ የተገለጹትን ውሣኔዎች ማሳለፋቸውን፣ እንደዚሁም ቃለ ጉባኤው ወደመዝገብ በትክክል መገልበጡን በሙሉ ስምና ፊርማችን እያረጋገጥን፣ በሰነዶቹ ላይ ስለተገለጹት ጉዳዮች እና ስለተላለፉት ውሳኔዎች ትክክለኛነት ስማቸው በሰነዶቹ ላይ በተዘረዘሩት ሰዎችም ሆነ በሌላ ጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወገን ለሚነሳ ማናቸውም የሙብት ጥያቄ ኃላፊዎች መሆናችንን ጭምር እናረጋግጣለን፡፡

| ተ/ቁ | ሥም | የተወከለ ከሆነ የተወካይ ሥም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | - | የቦርድ አባል | |
| 2 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻግሬ | - | የቦርድ አባል | |
| 3 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | - | የቦርድ አባል | |
| 4 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | - | የቦርድ አባል | |
| 5 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | ወ/ሮ ዓይናለም አሸብር | የቦርድ አባል | |
| 6 | ወ/ሮ አዜብ በቀለ | - | የማሕበሩ ፀሐፊ | |

NATIONAL BANK OF ETHIOPIA 53

ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት
ቅ/10 ጽ/ቤት አ/አ
ተሚው በጽ/ቤቱ ቀርበው ፈርመዋል።

Documents Authentication & Registration Service Branch ... Office

የሰነዶች ማረጋገጫና
ምዝገባ አገልግሎት
አዲስ አበባ (የቅርንጫፍ አስር ጽ/ቤት)

የቴምብር ቀረጥ ማረጋገጫ ማህተም

የተከፈለበት ምክንያት 121
የገንዘብ ልክ ብር
በፊደል
ወይም ብር ___ የከፈለበት ደረሰኝ ቁጥር
ቀን 20 ___ ዓ.ም
የቴምብር ቀረጥ ሰብሳቢ አስፈፃሚ
ስም
ፊርማ

# ፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ
## የባለአክሲዮኖች 26ኛ መደበኛ ጉባዔ
## የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (attendance sheet)

| ተ.ቁ | ስም ከነአያት | አድራሻ | የአንዱ አክሲዮን ዋጋ (በብር) | የአክሲዮኖች ብዛት: ያላቸው የአክሲዮን መጠን | የተፈረመ | የተከፈለ | ያልተከፈለ | የድምጽ ቁጥር | የባለአክሲዮኑ ወይም የወኪሉ ስምና ፊርማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጌታቸው ወርቁ ወ/ማርያም | አ.አ. ቦሌ ክ/ከ ቀ. 02 የቤት ቁ. 893 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | የለም | 2,500 | |
| 2 | አቶ ማሞ ከበደ ሽንቁጥ | አ.አ.ጉለሌ ክ/ከ ቀ. 19 የቤ.ቁ. 703 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 3 | ዶ/ር አሰፋ ወ/ጊዮርጊስ ይልማ | አ.አ. ቦሌክ/ከ የቤ.ቁ. 711 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | ያልተገኙ |
| 4 | አቶ መስፍን ተፈራ ወ/ገብርኤል | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 03 የቤ.ቁ. 1843 | 1,000 | 2,452 | 2,452 | 2,452 | “ | 2,452 | |
| 5 | ወ/ሮ ፀሀይ ፀጋዬ መከተ | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 13/14 የቤ.ቁ. 092 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 6 | ወ/ሮ ሰበሰች ጸጋ ባለህ | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 13/14 የቤ.ቁ. 100 | 1;000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 7 | ወ/ሮ ጽጌ ሃይሌ ወ/ጊዮርጊስ | አ.አ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ቀ.12/13 የቤ.ቁ 415 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 8 | ወ/ሮ አለምነሽ ኃ/ማርያም ባዲሾ | አ.አ. የካ ክ/ከ ቀ. 08/15 የቤ.ቁ. 350 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 9 | አቶ ኤፍሬም አላምረው ቦጋለ | አ.አ. ልፈ ቀራንዮክ/ከ ቀ. 15/16 የቤ.ቁ.38/137 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 10 | አቶ ተዘራ ከበደ በቀለ | አ.አ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ቀ. 15 የቤ.ቁ. 1287 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 11 | አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ | አ.አ. ቂርቆስ ክ/ከ ቀ. 03 የቤ.ቁ. 379 | 1,000 | 129 | 129 | 129 | “ | 129 | |
| 12 | ወ/ሮ ፍሬህይወት ገበየሁ ስሚነው | አ.አ. ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ.ከ ቀ 04 የቤ.ቁ. 1191 | 1,000 | 81 | 81 | 81 | “ | 81 | |
| 13 | ሲ/ር መሠረት ሺፈራው ይብራሁ | አ.አ. ቦሌ ክ/ከ ቀ. 19/19/20 የቤ.ቁ. 616 | 1,000 | 81 | 81 | 81 | “ | 81 | ያልተገኙ |
| 14 | ወ/ሮ ሰላማዊት አበበ ተጫኔ | አ.አ. አራዳ ክ/ከ 2 ቀ.10 የቤ.ቁ. 184 | 1,000 | 81 | 81 | 81 | “ | 81 | ያልተገኙ |
| 15 | ወ/ት ፍላጎት ለማ ክብረት | አ.አ. አዲስ ከተማ ክ/ከ ቀ. 19/20 የቤ.ቁ. 099 | 1,000 | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| 16 | አቶ አክሊሉ ታደሰ አሻሚ | ሻሸመኔ ወ. 2 ቀ. 05 የቤ.ቁ. 411 | 1,000. | 2,500 | 2,500 | 2,500 | “ | 2,500 | |
| | ድምር | | | | 30,324 | 30,324 | | 30,324 | |

እኔ የፒስ ማይክሮፋይናንስ አ.ማ. የማህበሩ ፀሐፊ ይህ የጉባኤው ተሳታፊዎች መመዝገቢያ ሰነድ (Attendance sheet) በጉባኤው በአካል የተገኙ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎች የፈረሙበት ስለመሆኑ በሙሉ ሥም እና በፊርማዬ በንግድ ህግ አንቀጽ 378 (2) መሰረት አረጋግጣለሁ፡፡

የማህበሩ ፀሐፊ ሥም ወ/ሮ [illegible] በቀለ ፊርማ፡ 